# ኢትዮጵያችን

*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ቁጥር 1 ጥቅምት ፳ ቀን ፪ ሺህ ፲፩ ዓ.ም.

## የ"ቀን ጅብ" በግ ላይሆን . . .

(ድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ https://www.youtube.com/watch?v=QA7F515m49U

እነሆ! "***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ከተመሠረትን መስከረም 8 ቀን 2011 ዓ.ም. ሁለት ዓመታችንን አስቆጠርን። በዚህ የሁለት ዓመት ጉዞ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ይዘን የተነሳውን ዓላማ በፕሮግራማችን (www.ethiopiachen.org) አሳውቀናል። በተለያዩ የሀገሪቷ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ጉዳዮችም ዝርዝር ባለ መልኩ በድርጅታችን ማንፌስቶ ዘግበን አስነብበናል። በትንሹ ለአለፈው ግማሽ ምዕተ ዓመት ምላሽ ያላገኙ ሀገራዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎችን አንግበን ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜትን ዋልታ ባደረገ መልኩ በትግል ላይ እንገኛለን። በዚህ አጭር የትግል ሂደታችን የሀገራችንን ወቅታዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ከጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በልሳናችን "***ኢትዮጵያችን***" አቅርበናል። በሀገሪቱ የተፈጠሩ አሳሳቢ ክስተቶችን በተመለከተ አቋማችንን አሳውቀናል። የሀገር ሉዓላዊነትና የጀግንነት ኢትዮጵያዊ አኩሪ ታሪካችንን በወቅቱ በመዘከር "ክብር ለሰማዕታት" ብለን ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ አድርገናል። በአገኘነው መገናኛ ብዙሃን ***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! አንድ ሰንደቅ ዓላማ!" ሰንል ለእኛ ኢትዮጵያችን፣ ሕዝባችንና ሰንደቅ ዓላማችን አንድም ሦስትም መሆናቸው የዓላማችን ምሰሶ መሆኑን አበክረን አስተዋውቀናል።***

በኢሕአዴግ አገዛዝ ዘመን፤ አገዛዙን በመቃወማቸውና ለየት ያለ አቋም በማስተጋባታቸው ለተንገላቱ፣ ለተሰደዱ፣ ለታሰሩ፣ ለተደበደቡ፣ ለተገደሉ ጮኸናል፣ ድምጻችንን አሰምተናል፣ ብዕራችንን ከወረቀት አገናኝተናል። ከኖሩበት ቀዬ በግፈኞች ያለ አግባብ ለተፈናቀሉ "የፍትህ ያለህ!" ብለናል። ሀገራችን ተቆርቋሪ እንዳይኖራት ትውልድን በጫት፣ በአደንዛዥ ዕጽ፣ በሺሻ፣ በመጠጥ፣ በሴተኛ አዳሪነት፣ በመጤ ፊልም ወዘተ የማደንዘዝና የማኮላሸት "ወያኔአዊ" ተልዕኮ ሀገርና ትውልድ እየገደለ መሆኑን ደጋግመን ገልጸናል። በኢሕአዴግ ላይ የተቀጣጠለው አካባቢያዊ ቁጣ ሀገራዊና ሕዝባዊ መልክ በመያዝ በተቀናጀ አካሄድ ያለውን የአመራር ክፍተት በመሸፈን ትግሉን ከተፈላጊው ግብ ለማድረስ የበኩላችንን ጥረት አድርገናል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለአለፉት 27 ዓመታት ቆላልፎ የያዛት የዘር ፖለቲካና ቋንቋንና ዘርን ተገን ያደረገ አከላለል ተወግዶ ማዕከሉ ኢትዮጵያዊነትን ያደረገ ሕገ መንግሥት ተግባራዊ ይደረግ ዘንድ የኢሕአዴግ አገዛዝን ታግለናል፣ እንታገላለንም። ዘርንና ሃይማኖትን ተገን ያደረገ የፖለቲካ ድርጅት ከአገዛዙ ማብቃት ጋር ያከትም ዘንድ ታግለናል፣ እንታገላለንም። የሀገራችን የግዛት ሉዓላዊነትና የሕዝባችን አንድነት እንደተጠበቀ የዜግነትና የግለሰብ መብትን ቀዳሚ ያደረገች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንድትመሠረት ታግለናል፣ እንታገላለንም። እጅግ ካሻቀበው የኑሮ ውድነት የተነሳ በቀን አንዴ መመገብ ለተሳናቸው ወገኖቻችን፣ ደሞዛቸው ከቤት ኪራይ አልዘል ብሏቸው አንጀታቸውን

አስርው ለሚቃትቱት ሠራተኞች፣ "ሲያጨሷት እየጨሰች. . ." ለሚሉት ብዙሃን ረሃብተኞች "የሀገር ያለህ! የሕዝብ ያለህ!" ብለን ታግለናል፣ እንታገላለንም። የሀገሪቷን አንጡራ ሀብት የዘረፉና ያለአግባብ የበለጸጉ ሙሰኞችና ሌቦች በፍርድ ይጠየቁ ዘንድ ታግለናል፣ እንታገላለንም። ማደሪያቸው ቱቦ፣ ምግባቸው የቆሻሻ ገንዳ፣ ቤታቸው እደጅ፣ ሳቃቸው ለቅሶ፣ ደስታቸው ሀዘን፣ ኑሯቸው ልመና፣ . . . ለሆኑ የአገዛዙ የ"ዕድገትና ልማት" ተምሳሌት ወገኖቻችን ኑሮና ሕይወት ይሻሻል ዘንድ ታግለናል፣ ዛሬም እንታገላለን።

የኢሕአዴግ አገዛዝ በሕዝባዊ አመጽ እየተናወጠ የመጨረሻው የጣር እስትንፋሱ ላይ በደረሰበት የዛሬ ስድስት ወር ገደማ ከአገዛዙ ብቅ ያሉትን የክቡር አቶ ለማ መገርሳን ቡድንና በቀጣይነት የጠቅላይ ሚኒስቴርነቱን የተረከቡትን የክቡር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን አመጣጥና ሂደት አስመልክተን በተደጋጋሚ አቋማችንን አሳውቀናል። ጠ/ሚ በአደረጉት ጥሪ መሠረት ትግላችንን ከነበረን ኀቡእ እንቅስቃሴ ብቅ በማድረግ የተገኘውን ሕጋዊ መድረክ ለመጠቀም በሀገር ቤትም በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን። ይዘን የተነሳነውን መሠረታዊ ሀገራዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎች ዝቅ ሳናደርግ በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ የደረሰውን 27 ዓመት አምባገነናዊና ዘረኛ አገዛዝ ለመታገል ማንነታችንን አሳውቀን ከምስኪኑ ሕዝባችን ጋር መከራና ችግሩን ተጋፍጠን የሀገሩ ባለቤት ይሆን ዘንድ የጀመርነው ትግል አሁንም በትግል ላይ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

ጠ/ሚ ዶር ዐቢይ አሕመድ በአለፈው 6 ወር ይዘው የተነሱትን ኢትዮጵያዊ አጀንዳና አካሄድ በመገምገም "***ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በተደረገው ጥሪ መሠረት በሀገር ቤት ለመንቀሳቀስ ስንወስን የ27 ዓመት የዘረኝነት አገዛዝን ልንታገል፣ ልናስወግድ እንጂ ሕዝባዊ ዓላማችንን ልንጥል እንዳልሆነ አበክረን እናሳውቃለን። የኢሕአዴግ የ27 ዓመት አገዛዝ በሀገሪቷ ላይ ያሳደገውን እጅግ የከፋ ውስብስብ ችግሮችን ይዞ በሀገራችን ኢትዮጵያ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ማለት "ህልም አለኝ በሰማይ፤ ውጤቱን የማላይ" ከማለት አይዘልም። *የ"ቀን ጅብ" በግ ሳይሆን ሌባን ይዞ ሩጫ መሠረታዊ ለውጥ ኢያመጣም።*

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየተካሄደ ያለው ለውጥ ኢሕአዴግ 27 ዓመት ያለአንዳች ተቀናቃኝ በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ ያደረሰውን መከራ ወደ ጎን አድርጎ በቀጣይ ምርጫ የአገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም እንዳይሆን ስጋታችንን ልናጋራ እንወዳለን። 27 ዓመት ያለ አንዳች ተቀናቃኝ በጉልበት፣ በማሳደድ፣ በማሰር፣ በመግረፍ፣ በመግደል አፍኖ የገዛ አገዛዝ ማብቃት ይኖርበታል ስንል የሕዝባችንን ምሬት ማስተጋባታችን ነው። ለዚህም ነው *የሀገሪቷንና የሕዝባችንን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመፍታት የሚቻለው ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች አካቶ በሚመሠረት የሽግግር መንግስት መሆኑን በድጋሚ ልናሰምርበት የምንገደደው።*

ኢሕአዴግ ቆላልፎ ያስቀመጠውን የምርጫ ቦርድ ተቋምና አሠራር ሳይወገድ፣ አፋኙ የሚድያና የፕሬስ ሕግ አዋጅ ሳይነሳ፣ ንጹሃንን ለማፈን ቀዳዳ የሆነው የአሸባሪነት አዋጅ ተግባራዊ እየሆነ፣ በመላው ሀገሪቷ የተሰገሰጉ የአገዛዙ ዘራፊዎች ዋናውን ሥልጣን ተቆናጠው፣ ህወሓት በዘመኑ ቆላልፎ ያደራጀው የ"አጋዚ" ጦርና የስለላ መረብ ሳይበጣጠስ፣ ለዴሞክራሲ ሂደቱ አስፈላጊ ተቋማት ሳይመሠረቱ፣ ሌላም ሌላ፤ ተፈላጊውን የሥርዓት ለውጥ ማምጣት ሊታሰብ እንደማይቻል ከራሳችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ መማር በቂ ነው።

በዓፄ ኃ/ሥላሴ ዘመን ባላባቱንና መኳንንቱን ይዞ "መሬት ለአራሹ" የሚታሰብ አልነበረም። በ1953 ዓ.ም. በንጉሡ ላይ የተሞከረው የታህሳሱ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ማስጠንቀቂያ ደወል ሆኗቸው

*ንጉሡ አጠገባቸው ያሉትን መኳንንትና ባላባት በማማከር ወደ መለስተኛ ጥገናዊ ለውጥ ከማምራት ይልቅ ጉዳዩ በወንድማማቾቹ መገደል ያበቃ ይመስል ንቀው ተዉት። በቀጣይነትም የሚከሰቱ ተቃውሞዎችን መጠኑም ቢያንስ በማፈንና በማስወገድ ሊጠቀሙ የተጓዙበት መንገድ ከ13 ዓመት በኋላ ሕዝባዊ ቁጣን አስነስቶ አሳዛኝ አወዳደቅ ወደቁ። ሥርዓቱ ተናደ። ዛሬ ታሪክ ነውና በነበር ይታወሳሉ።*

*መሪ ያጣውን የየካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት ተገን አድርጎ ብቅ ያለው ደርግ ገና ከጅምሩ 60ዎቹን በመረሸን አብዮቱን ሲበላው ሦስት ወር አልፈጀበትም። ከወታደራዊ አገዛዝ ወደ ኢሠፓ እራሱን ቀይሮ ሲያጓራና ሲገድል የኖረው ደርግ በግንቦት 1981 ዓ.ም. በራሱ የበላይ መኮንኖች የተሞከረበትን መፈንቅለ መንግስት አክሽፎ በግድያው ዳግም አቅራራ እንጂ "ምን መደረግ አለበት?" ብሎ ሊጠይቅም፣ ሊያስብም ፍላጎት አልነበረውም። ገዳይ ይዞ ለውጥ የለምና ከዚህ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ሁለት ዓመት ሲያጣጥር ከርሞ ደርግ ኢሠፓ ወደ መቃብር ተወረወረ። የደርግ የአንድ ሳንቲም ገጽታ የሆነው ህወሓት ከፋሽስታዊ አምባገነን ሥርዓት ወደ ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ሀገሪቷን ወሰዳት።*

*አራተኛው መንግሥትስ? እውን ኢሕአዴግን እንደያዘ በለውጥ ስም ይቀጥላል ወይስ...? እውን ኢሕአዴግ ከስድስት ወር በፊት ሊውጠው የተነሳውን ሕዝባዊ ማዕበል በመመልከት ለመሠረታዊ ለውጥ ተዘጋጅቷልን? ጠ/ሚ ዶር ዐቢይ እውን የኢትዮጵያ ሕዝብና የሀገራችን ችግር ሊፈቱ የተነሱት ስለ ኢትዮጵያዊነት በመስበክ ብቻ ነውን? ኢሕአዴግ የሰጠንን በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት የመከፋፈልና የማባላት 100 ዓመት የቤት ሥራ ተመልክተውታልን? ኢሕአዴግ አሁን ያገኘውን ዕድል ሊጠቀምበት ካልቻለ ሕዝባችን ለብሶቱ ምላሽ፣ ለሀገሩ ደህንነት ግምባሩን አያጥፍምና ከላይ እንደጠቀስናቸው አገዛዞች አይወድቁ አወዳደቅ ዕጣው እንደሚሆን ፖለቲካውን ለተገነዘበ በቂ ምልክት ነው።*

***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"** በወቅቱ የሀገራችን ፖለቲካዊ ሂደት ላይ አንዳንድ ነጥቦችን በማንሳት አሁን ያለው የኢሕአዴግ አገዛዝ ማድረግ ያለበትን እየጠቆምን "ጅሮ ዳባ ልበስ" ለሚል አገዛዝ ሕዝባዊ ትግሉ ተጠናክሮ ለድል የሚበቃበትንም መንገድ እናመላክታለን።*

<u>*የዘርና የቋንቋን ፖለቲካ በተመለከተ፦*</u>

*ኢትዮጵያ ሀገራችንን ለከፋ ችግር የዳረጋት የህወሓት/ወያኔ በዘርና በቋንቋ ሀገሪቷን የከፋፈለ ሕገ መንግስትና ቋንቋን ተገን ያደረገ ፌደራል አስተዳደር የሥርዓቱ ዋነኛ መለያ ነውና በተፈጥሮአዊ አቀማመጧ ወይም በጥንቱ ክፍለ ሀገር/አውራጃ አስተዳደር ሊተካ የሚችልበትን አቅጣጫ በውይይትና በምክክር ተግባራዊ ለማድረግ መጣር ይኖርበታል። ለዚህም "**ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**" በድርጅታችን የተዘጋጀውን የሀገራችንን አማራጭ አስተዳደራዊ አወቃቀር አስመልክቶ ከሌሎች ሠነዶች ጋር ለጠ/ሚ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ አሜሪካ በመጡ ወቅት አቅርበናል።*

*በተለይ ህወሓት/ወያኔ ለ27 ዓመት የዘራው የዘር ፖለቲካ በኦሮሞ ልጆች ዘንድ እጅጉን አቆጥቁጧል። ኢትዮጵያን እንዲጠሉ፣ ቋንቋዋን እንዳይናገሩ፣ ባህሏን እንዳይጋሩ፣ ሰንደቅ ዓላማዋን እንዲረግጡ፣ ጀግኖቿን በጠጥ ቀራጭነት እንዲፈርጁ፣ አማራና ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት እንዲሰነዝሩ፣ ሀገር ገንጥለው "ኦሮሚያ" እንዲሉ . . . እጅጉን ተዘምቷል፤ ተሠርቷል። ወያኔ/ህወሓት የዘራው መርዝ ዛሬ በኦሮሞ ልጆች ዘንድ የ"ትውልድ" ጥያቄ እንዲሆን አድርጎታል።*

*ለዚህ ደግሞ ለኢትዮጵያ አንድነት የሚሞግቱ ኃይሎች የርስ በርስ ሽኩቻና አለመደማመጥ፣ አለመስማማት ብሎም እየተዳከመ መምጣት የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል።*

*በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ጥራዝ ነጠቅ ፖለቲከኞች ግፊት በኦሮሞ ወገኖች በኩል የሚታየውና እየተባባሰ የመጣውን ኢትዮጵያን የመበታተን አደጋ መከላከያው ጉልበትና ጦርነት ሊሆን አይችልም። ሁኔታው ሲግል፣ ሲጠነክር ማህበራዊ/ሶሻል ሚድያን፣ ኢንተርኔት አገልግሎት መዝጋት የመፍትሄ አካል አይሆንም። በሌላም በኩል ዘረኝነትን በማጠናከር እንደማይሆን ለወያኔ/ህወሓትም አልበጀምና "የለውጡ" አራማጆች ልብ ሊሉት ይገባል። የዘር ድርጅትን ወደ ፓርቲ ማሳደግ ዘረኝነትን ዳግም ማደስ ሲሆን ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ አጀንዳን ዝቅ እንደሚያደርግ ልንገነዘብ ይገባናል።*

*ደግመን ደጋግመን እንዳሳሰብነው አሁንም መፍትሄው መነጋገርና መግባባት ነው። ኢትዮጵያ ያለ ኦሮሞ፣ ኦሮሞ ያለ ኢትዮጵያ ሕይወታቸው በድን እንደሆነ የሚያስደምጥ መድረክ ሊገኝ ይገባል። ሁሉም ዘሮች ለኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያም ለሁሉም ልጆቿ፣ ሁሉም ቋንቋ የኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያም የቋንቋ ባለሀብት መሆኗን ለማጉላት ያገባኛል ከሚሉት የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራትን፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን፣ የሃይማኖት አባቶችን ይዞ መምከር አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ የሀገራችን ነገድ/ጎሳ የራሱ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ይቅር የመባባያና የመታረቂያ ሀብታቸውን ልንጠቀምበት ይገባል። ተጣመው የተሰበኩ ታሪኮች እንዲቃኑ፣ ኢትዮጵያን በጋራ እንድንጠብቃት፣ ሰንደቅ ዓላማዋ የአንድነቷ ተምሳሌት መሆኑን፣ ጀግኖቿን ልንዘክር፣ ልናጎላ የምንችለው ያለንን ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴት ተጠቅመን ልንመክር ሲቻል መሆኑን ልንጠቁም እንፈልጋለን።*

***<u>አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፦</u>***

*በአንዳንድ ጽንፈኞች ወይም* 27 *ዓመት በተሰበከው የተጣመመ ታሪክ አምነውበት በመስከረም አጋማሽ አዲስ አበባ ላይ ሊደርስ የነበረው ጥቃት የታሰበውና የታቀደው ብልጭታ ነው ቢባል ያስኬዳል። ሊሠመርበት የሚገባው ጉዳይ አዲስ አበባም ሆነ የኦሮሚያ ግዛት የኢትዮጵያ አካል እንደሆኑ ነው። በአንቀጽ* 39 *ምሰሶ የቆመው የወያኔ/ኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት ትግራይ፣ አፋር፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል፣ ኦሮሞ፣ ጋምቤላ፣ ደቡብ ሕዝቦች፣ ሶማሌ እያለ ሊገነጣጥለን መሠረቱን የጣለው የዛሬ* 27 *ዓመት ቢሆንም በውስጡ ያሉ ልጆቿ የደም ትስስር "ኢትዮጵያዬ" በሚል ጩኸታቸው ባዶ ገጽ አድርገውታል። ያደርጉታልም።*

*በአዲስ አበባ በተለይ ቡራዩ ቅዳሜ መስከረም* 5 *ቀን* 2011 *ዓ.ም. በከፋ መልኩ የተካሄደውን እጅግ አሳዛኝ ጭፍጨፋ፣ ግድያ፣ ንብረት ማውደም ያስከተለው በከተማዋ የተሰቀሉ አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችንን በማውረድና ብሎም በማቃጠል ሊፈጸም ለተቃጣው እምዬ ኢትዮጵያ ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ከመከላከል የመነጨ ነው። ኢሕአዴግ ከ*27 *ዓመት ሀገር የማጥፋት የረቀቀ ተልዕኮው ሌላው ገጽታ በተለይ የአዲስ አበባን ሕዝብና ወጣቱን መቀጥቀጥና ማዳከም ነበር። በልማት ስም ከተወለዱበት አካባቢ እየተፈናቀሉ የተወረወሩ የአዲስ አበባ ቤተሰቦችና ወጣቶች ለጎዳና አዳሪነት ተዳርገዋል። በሀዘን፣ በደስታ እየተረዳዳና እየተደጋገፈ የኖረውን የአዲስ አበባ ኅብረተሰብ ዛሬ እንዳይገናኝ ተደርጎ በየዳሩ ተበትኗል። እናቶች አቅም ኖሯቸው የዕለት ችግራቸውን እንዳይወጡ የየአካባቢው ጉልታቸው በጊዜው ዘራፊዎች ተነጥቀዋል። ከተማዋ እጅግ ካጨናነቃት የሕዝብ ብዛት አንፃር ሰላሟን የሚያደፈርስ የአገዛዙ የረቀቀ ትንኮሳ ከሌለ በቀር የአዲስ አበባ ነዋሪ ተከባብሮና ተዛዝኖ፣ ረሃቡን አስታግሶ የሚኖር ኅብረተሰብ ነው።*

*በከተማዋ እጅግ በጣም ሴተኛ አዳሪዎች፣ ያለ እድሜያቸው በገላቸው ኑሮን ለመግፋት የተገደዱ ሕፃናት ተበራክተዋል። ለባለ ቱጃሮችና ሴሰኞች ሴቶች እህቶቻችንን መደለል የገቢ ምንጫቸው ያደረጉ የአገዛዙ ሰለባ ወጣቶችም ጥቂት አይደሉም።*

*በተለይ ምርጫ* 1997 *ዓ.ም. ምክንያት አድርጎ ህወሓት የአዲስ አበባን ሕዝብ ለመቅጣት ባወጣው "መሠሪ ፖሊሲ" መሠረት ለማየት በሚዘገንን መልኩ የቅጣቱ ሰለባ ሆኗል። ከየመንገዱ ዳርና ዳር እተከመሩ ቆሻሾች ውስጥ ምግብ ፈላጊውንና የሚጸዳዳውን መመልከት ኀሊና ያቆስላል። ለልማት ተብለው በትንሹ ከአራት ዓመት በፊት የፈረሱ አካባቢዎች ቆሻሻ መጣያ፣ መጸዳጃ፣ መተኛና መመሸጊያ ሆነው ሲታዩ እውን ልማት? ወይስ ጥፋት? ያሰኛሉ።*

*አዲስ አበባ ይህን ሁሉ መከራ ተሸክማ፣ የተለያዩ ዘሮችን ይዛ በሀገርና በሰንደቅ ዓላማው ፍንክች የማይል ኅብረተሰብ ታቅፋለች። በረሃብ ያንቀላፋው ወጣት ሰንደቅህ! ሲሉት ይባንናል፤ ተስፋ ቆርጦ የተከራመተው ወጣት ሀገርህ! ሲሉት ዘራፍ! ይላል። ከነድህነቱ ኢትዮጵያዊነትና ሰንደቅ ዓላማውን የወደደ፣ ከፍ ያደረገ ብቻ ሳይሆን የታሠረ፣ በየእሥር ቤቱ የተጋዘ፣ የተደበደበ፣ የተገደለ ትውልድ። ሰንደቅ ዓላማዬን አላስረግጥም ብሎ ለእስር የተዳረገ ዜጋ። "ቦዘኔ፣ ወያላ. . . ብሎ ለሀገር አሳቢ" ተብሎ በአገዛዙም፣ በአጥቂዎቹም የጥቃት ሰለባ በመሆን ዛሬም በየእሥር ቤቱ ሲማቅቅ ማየት "አይ ለውጥ!" ያሰኛል። ዛሬም እንደትላንቱ "መሣሪያ ሊቀሙ ሲሉ" ተብሎ ይወነጀላሉ።*

***"አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** *በቡራዮና በሌሎችም የአዲስ አበባ አካባቢዎች በቅርቡ ለደረሰው ጥቃትና ፍጅት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለጽን የኢሕአዴግ አገዛዝ በአዲስ አበባ ወጣቶች ላይ ያደረሰውን ጉዳትና የእሥር እንግልት አጥብቀን እናወግዛለን። በመሆኑም ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በእሥር ያሉ የአዲስ አበባ ወጣቶችን ጨምሮ ሌሎች ፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ዘንድ አጥብቀን እንጠይቃለን። አጥፊዎች ለፍርድ ይቅረቡ እሚል ቅዠት ውስጥ የማንገባው ኃላፊነቱ ሀገሪቷን የሚያስተዳድረው አገዛዝ በመሆኑ "ለፈራጅ ፍርድ ይስጠው" እንላለን።*

*ጩኸታችን ስለ ሰው ልጅ መብት ነውና ቀደም ሲልም በሶማሌ ክልል በኦሮሞ ወገኖቻችን ላይ የደረሰውን አሳዛኝ ፍጅትና መፈናቀል እጅጉን እናወግዛለን። በደቡብ ኢትዮጵያ ወገኖቻችን የሚደርሰውን ግፍ፣* 27 *ዓመት ሙሉ እንደተቀጠቀጡ ያሉትና በቅርቡ ዳግም ድረሱልን ጩኸታቸውን ለሚያሰሙት የጋምቤላ ወገኖቻችን አለንላችሁ እንላለን። የጥቂያችሁ መልስ ሩቅ አይሆንምና ጽናታችሁ ትግሉ ይሁን፣ ኩራታችሁ ሀገራችሁ ትሁን እንላቸዋለን። ኢትዮጵያን ለማጥፋት አማራ ላይ ማነጣጠር በሚል ቅዠት ከህወሓት ሥልጣን መጨበጥ ጊዜ አንስቶ ዛሬም እየተጨፈጨፈ ያለው አማራ የእልውና ጉዳይ ነውና እራሱን ለመከላከል የሚያደርገው መሰባሰብ በተቀናጀ መልኩ መቀጠል እንደሚኖርበት ድጋፋችንን እናሰማለን።*

*<u>የኤርትራን ጉዳይ አስመልክቶ፦</u>*

***"አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** *በወያኔና ሻቢያ ቅንብር የተካሄደውን ኤርትራን የመገንጠል ጉዳይ በአግባቡ አለመካሄዱን በማንፌስቷችን ላይ ገልጸናል። ይህ* 27 *ዓመት ያስቆጠረ የኤርትራ ጉዳይ ከትውልድ መተካትና ከጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ኤርትራን እንደ ሀገር መቀበሉን ብንጋራም የአሰብ ወደብ ጥያቄአችን ግን አሁንም አየር ላይ ያለ ነው። በወያኔ/ህወሓት/ሻቢያ ኢትዮጵያን የማዳከም ቅድመ ዝግጅት አንፃር ሀገራችን ወደብ አልባ እንድትሆን የተሠራው አሳፋሪ ስህተት ሁለቱ መንግስታት ይቅር ከተባባሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ*

አሰብ ለሀገራችን ኢትዮጵያ መመለስ ይኖርባታል ባይ ነን። ይህም የራዕያችን አንዱ አካል እንደሆነ ልንገልጽ እንወዳለን።

የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በባህልና በሃይማኖት የተሳሰሩ እንደመሆናቸው መጠን ዳግም ሁለቱን ሀገራት ለማቀራረብ የሚደረገውን ጥረት የምንደግፈው ይሆናል። ሆኖም በማንኛውም መልኩ የኤርትራ/ሻቢያ በሀገራችን ጉዳይ ጣልቃ የመግባት አዝማሚያን አበክረን እንቃወማለን። በቅርቡም በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኤርትራውያን ወደ ኢትዮጵያ የመፍለስ ጉዳይ ለምን እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም አሳሳቢና ሊጤን የሚገባው መሆኑን ሳንገልጽ አናልፍም።

## *ወደ ሀገር ቤት ስለገቡ የፖለቲካ ድርጅቶች፦*

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በአደረጉት ጥሪ መሠረት ***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** የውጭ አመራር አካል ነሐሴ 26 ቀን 2010 ዓ.ም. (September 01, 2018) ኢትዮጵያ አዲስ አበባ መግባታችን ይታወቃል።

አመራሩ ሀገር ቤት ካሉ አካላቱ ጋር ከሚያደርገው እንቅስቃሴ በተጨማሪ በኢሕአዴግ ምርጫ ቦርድ ደንብ መሠረት የፖለቲካ ድርጅቶችን ለማስመዝገብ በተሰጠው የግማሽ ቀን መግለጫና ማብራሪያ ተሳታፊና ተካፋይ ለመሆን ቢቻልም ጉዳዩ እስካሁን በእንጥልጥል ያለ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

በተጨማሪም ሀገራዊ መግባባትና ትብብር በሚል በዋሽንግተን ሲያትል በፌብሩዋሪ የተካሄደው 26 የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባኤ ቀጣይ ሂደትን አስመልክቶ በተጠራው ስብሰባ ድርጅቱን ወክለን ለመገኘት ችለናል።

በጥቅሉ ወደ ሀገር የገቡትንና የሚገቡትን የፖለቲካ ድርጅቶች በምን ዓይነት የመረጃ ምንጭ ሰንሰለት አስፈላጊውን ጉዳይ ማስፈጸም እንዳለባቸው ግልጽ አይደለም። ለአንዳንዶች ሜዳውና ፈረሱ እጅግ ቀላል ሲሆን እራሳችንን ጨምሮ ሌሎች ደግሞ ዳር ዳሩን እንዲሄዱ የተፈረደባቸው ይመስላል። የመገናኛ ብዙሃን፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች የገቡትን የፖለቲካ ድርጅቶች ለማስተዋወቅ መስፈርታቸው ወይም መመሪያቸው ምን እንደሆነ ምስጢር የተላበሰ ነው። በጥቅሉ አገዛዙ እውን ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን በተላበሰ መልኩ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ይንቀሳቀሱ ዘንድ ምኞቱ ከሆነ ላንዱ የተለቀቀ በር ለሌላውም ክፍት መሆን እንደሚገባው እናስገነዝባለን።

በተጨማሪም 27 ዓመት ኢሕአዴግ/ህወሓት የተመራበትን አግላይ ፖለቲካ አሁንም ቀጣይነት ካለው በእርግጠኛንነት "ድንቄም ዴሞክራሲ" ሲጨመርም "መለወጥ ወይስ መገላበጥ" ማለት በቂ ነው። የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት መሠረቱ ሕዝብ ነውና ድጋፍ እስካልተቸረው ድረስ ምርጫ ቢሉት ሌላም የትም አይደረስምና አግላይነቱን ለሕዝብ እንተወው። ". . . ምን ያለበት ዝላይ አይችልም" እንዳይሆን በሌሎች ላይ ፈራጅ ለመሆን የሰለቹ "አዲስ ነው የቆየ፣ ትንሽ ነው ብዙ፣ ሕጋዊ ነው ሕገወጥ" አባባሎችን ወደ ጎን አድርገን ሚዛኑን ለሕዝቡ እንተውለት።

## አዲሱ የሚኒስቴሮች ሹመት

ጠ/ሚ ዶር ዐቢይ አሕመድ ሥልጣን ላይ ብቅ ባሉ 6 ወራት ለሁለተኛ ጊዜ የሚኒስቴሮቻቸውን ሹመት ማክሰኞ ጥቅምት 6 ቀን 2011 ዓ.ም. በተወካዮች ምክር ቤት አቅርበው አፀድቀዋል። የዛሬ ስድስት ወር ለተሾሙት "ቆይ እስቲ ጊዜ እንስጣቸው" ያልነው ሳይደርቅ ዛሬም አዲስ ተሹመውልን የምስንሰጠው ጊዜም እየተሟጠጠ መጥቷል። በዚህ የሚኒስቴሮች ሹመት ላይ ጠ/ሚ ዶር ዐቢይ የሴቶችን ተሳትፎ ለማጉላት ያደረጉትን ጥረት እያደነቅን ኢሕአዴግን ከማጠናከር አንጻር የአሻሿሙ ፖለቲካዊ ሂደት ጥያቄ እንደሚያስነሳ እንገነዘባለን።

"በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ ቢለጥፉት ይሆናልን?" እንዳለው መጽሐፉ በተቀዳደደ ሥርዓት ላይ የሚደረግ ሹመት ቤቱን በአሸዋ ላይ ከሠራው ቢመሳሰል አያስደንቅም። ከላይ እስከ ታች ሙስናና ሌብነት ድር ያደራባቸውን መንግስታዊ ተቋማት ሊያቃናቸው የሚችል አንድ ብቸኛ መንገድ የሥርዓት ለውጥ ነው እንላለን።

በአፋኝነቱ፣ በአሰቃይነቱ፣ በዘልዛይነቱ የሚታወቁ የደህንነት አካላትን ከነጉደኞቹ ይዞ ጉዞ ብቻ ሳይሆን በሚኒስቴር ደረጃ ማዋቀሩ "ፍትህ" ወዴት ልታመራ እየተንደረደረች እንደሆነ ጠቋሚ ነው። በሀገራችን ኢትዮጵያ ሰላምን ያደፈረሰው የኢሕአዴግ አገዛዝ እንጂ ሕዝብና የፈረደበት ወጣት አይደለም። መንግስት ሲያፍን፣ ሲያስር፣ ሲደበድብ፣ ሲገድል፣ ሲያሳምም፣ ሲያደነቁር፣ ሲያስርብ፣ ሲዘርፍ፣ ሲያሰድድ፣ በዘርና ሃይማኖት ሲከፋፍል፣ ባንዲራን ጨርቅ ሲል፣ ሐውልትን ድንጋይ ሲል፣ ጀግናን ጡት ቆራጭ ሲያሰኝ፣ ታሪክን ሲያናንቅ፤ "እምዬን፣ ማንነቴን፣ መመኪያዬን፣ መብቴን" ያለ ሕዝብና ወጣት ያምጻል፣ ሰላም ይደፈርሳል። አገዛዙ የጫረው እሳት ሲፈጀው ዳግም እንዳይነሳ ለማፈን የ "ሰላም ሚኒስቴር" በሚል የፖሊስ አካላትን ጨምሮ በተቀናጀና በተጠናከረ መልኩ ማዘጋጀት ለሕዝብ ሳይሆን በሕዝብ ላይ የሚመጣ አደገኛ አካሄድ እንደሚሆን አስቀድመን ለመግለጽ እንወዳለን።

## ምን መደረግ አለበት?

በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለይ ለአለፉት 27 ዓመታት ለተፈጠሩ ዘርንና ቋንቋን ማዕከል ላደረጉ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ምስቅልቅሎች ከኢሕአዴግ/ህወሓት ሌላ ማንም ተጠያቂ ሊሆን አይችልም። ሙሉ 27 ዓመት ያለምንም ተቀናቃኝ በማጭበርበር፣ በጉልበት፣ በደም፣ 99.6%፣ 100% "በማሸነፍ" የገዛ ብቸኛ አገዛዝ ነበርና። በዚህ ብቸኛ የኢሕአዴግ አገዛዝ ለጥፉ በርካታ ሕይወቶች ማንም ሊጠየቅ አይችልም፤ መንግሥት ነውና። ከሥራቸው፣ ከመኖሪያ ቄያቸው፣ ከመንደራቸው እየተፈናቀሉ ሚላስ ሚቀመስ በማጣት ለሴተኛ አዳሪነት፣ ለቦዘኔነት፣ ለእንግልት ለተንገላቱ ዜጎቻችን ከአገዛዙ የ"ቀን ጅቦች" ሌላ ማን ሊጠየቅ ይፈለጋል? የሀገሪቷ ኢኮኖሚ እጅግ አሻቅቦ በጥቂቶች አስረሽ ምቺው ሀገር ስትታመስ፣ በሕፃናት ጡጦ ፎቅ የገነቡ መንግሥታዊ ዘራፊዎችን ሕግ ካላየ ምኑን ለውጥ ተባለ?

አዎ! "ጊዜ እንስጠው" አባባል ለጠገበ፣ ክትፎን በደብል ብላክ ለሚያወራርድ፣ በቁርጥ ላይ ጥብስ ለሚጨምር አይሰማውም። ዝርፊያ አእምሮውን አደንዝዞት በየጉራንጉሩ ሕፃናትን ለሚያማግጥ ሴሰኛ "ጊዜ እንስጠው" ይስማማዋል። ሀገርና ሕዝብ በዘርና ሃይማኖት ሹክቻ ታምሰው "ብለን ነበር" ለማለት ላደፈጡ የ"ሥልጣን ጅቦች" "ጊዜ እንስጠው" ይመቻቸዋል። አዎ! ታጋሹና አስተዋዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ ወጣቱ ጊዜ ሰጥቶ ማየቱ ዳግም ለእስርና ለእንግልት እየዳረገው ይታያል።

የሕዝባችንና የከተሜው ረሃብ፤ ቁርስ በልቶ ለምሳ እንደሚንሰፈሰፈው ስግብግብ ሳይሆን፤ መብላት ከተባለም ቁርሱን ያሞ ምሳና እራት አጣምሮ ሚቀምስ ነው። ይህን አንጀቱን አስሮ ለሀገሬ አንድነት ከሆነ፣ ለሰንደቅ ዓላማዬ ክብር ካስገኘ፣ ከመታፈን ካገገምኩኝ ያለ ሕዝብ የተሞኘ የመሰላቸው ሞኞች ካሉ እንዲያስቡበትና ቀና ብለው እንዲያዩ እናሳስባለን።

ጠ/ሚ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ብቅ ካሉበት የ6 ወራት ጊዜ ወዲህ የታዩ በጎ ጉዳዮች ቢኖሩም በእርግጠኝነት ለመናገር ሀገሪቷ የገባችበትና ያለችበት ውስብስብ ችግር በሚገባ ሊጤን ይገባዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ "ኢትዮጵያዬ" ብቻ ስለተባለ የሀገሩ ችግር ይፈታል ማለት አይደለም። 27 ዓመት የጠማው የእምዬ ሀገሩ ስም ከፍ ማለት ቢያስደስተውም በስሟ እየዘመሩና እየጮኹ፣ ሰንደቋን እያውለበለቡ የቀበሩትን የቅርብ ጊዜ ገዳዮቹን እንደማይዘነጋ ልብ ልንል እንገደዳለን። መሠረታዊ የሀገሪቷን ችግሮች የሚቃኝና የሕዝባችን ዋና ዋና ችግሮች በተለይ የምግብ ሰቀቀን ውስጥ የገባበትን ስብህና ገዳይ ረሃብ እንዴት መፈታት እንዳለበትና የሠራተኛውና የደሞዝተኛው የኑሮ ደረጃ ሊስተካከል የሚችልበትን አቅጣጫ በአጭር ጊዜ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ከሁሉም ኃይሎች ጋር ጥረትና ምክክር ያስፈልጋል እንላለን።

በዚህም መሠረት

1. በተለይ ሀገሪቱ ከገባችበት ዘርንና ቋንቋን ተገን ካደረገ አከላለልና ዘረኝነት አገዛዝ ወጥተን ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ይገነባ ዘንድ የሀገሪቱን ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶች ባማከለ መንገድ ለሕዝብ ክፍት የሆነና ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ተሳታፊ የሚሆኑበት የውይይትና የመግባቢያ መድረክ ብሎም ለብሔራዊ ዕርቅ በር ከፋች መድረክ ማዘጋጀት ይጠቅማል እንላለን።
2. በኢሕአዴግ ዙሪያ የተሰባሰቡ የዘር ድርጅቶችን ወደ ፓርቲ ማሳደጉ ዘረኝነትን ይበልጥ ገኖ ይወጣ ዘንድ በር ከፋች መሆኑን በመጠቆም ኅብረ ብሔራዊ ሀገራዊ ድርጅቶች ይኀለብቱ ዘንድ እንጠቁማለን።
3. ኢሕአዴግን ማዕከል ያደረገ የፖለቲካ ድርጅት በማዋቀር ለቀጣይ ምርጫ ኢሕአዴግን ለማስቀጠል የሚደረገው ጥረት በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ ዳግም የጭቆናና የዘረኝነትን በትር ለማሳረፍ መሆኑን አስቀድመን ለማስገንዘብ እንቃጣለን።
4. አሁንም ለዚህ ሁሉ አማራጭ መፍትሄው ኢሕአዴግ ለ27 ዓመት ያለማንም ተቀናቃኝ ሀገሪቷንና ሕዝቡን ማዳከሙን ተቀብሎና እንደማንኛውም ድርጅት እራሱን አስቆጥሮ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶችና የሚመለከታቸውን አካላት ያካተተ የሽግግር መንግሥት መሥራች ኮሚሽን በማቋቋም ለወደፊት የምርጫ ሂደት ጥርጊያ መንገድ በቀናነት ይዘረጋ ዘንድ "***ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ጥሪያችንን እናቀርባለን።
5. በኢትዮጵያ አንድነት የማያወላዳ አቋም ያላቸው ተፎካካሪና ታጋይ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ፦ የኢሕአዴግ 27 ዓመት ብቸኛ አገዛዝ በሀገራችንና ሕዝባችን ላይ ያደረሰው ጥፋት ከበቂ በላይ ነውና እንደማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ሥልጣኑን ለሌሎች ያጋራ ዘንድ ለማስገደድ የተጠናከረ ድርጅታዊ አንድነት መመሥረት የወቅቱ አጣዳፊ ጉዳይ ነው እንላለን። በመሆኑ "እኛ ብቻ ተቃዋሚ፣ እኛ ብቻ ታጋይ" ለማንም አልበጀምና ወደ አንድ የጋራ መሰባሰቢያ መድረክ ትመጡ ዘንድ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ስንል እንወተውታለን።

***ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ***

***ለግማሽ ምዕተ ዓመት በችግርና በመከራ ኖረሃል። ያላቋረጠ ልጆችህን ነጠቃ በግፈኞችና በአምባገነኖች ተካሂዶብሃል። አንዱ በሀገርህ እየማለ ሌላው ሀገርህን ተረት ተረት እያለ ተለጉመህና ታፍነህ ኖረሃል። የግፉ ክምር ከጊዜ ወደ ጊዜ ኑሮህ የቁም ሞት እየሆነ፣ ምግብን በእጅህ ሳይሆን በዓይንህ፣ በጥርስህ ሳይሆን በስሜትህ፣ በውንህ ሳይሆን በእልምህ ታጣጥም ዘንዳ ዛሬ ያለህበት ደረጃ አድርሶሃል። ሚበሉት ሳይኖራቸው አይሄዱም፣ አይመጡምና ልጆችህን ወደ ትምህርት ከመላክ አንተንና ቤተሰቡን ይረዱ ዘንድ ያለ እድሜያቸው፣ በጨቅላነታቸው ለአደባባይ እንዲወጡ ተገደሃል። የነሱ የልጅነት ገመድ ዝላይ፣ ቅብብሎሽ፣ ሩጫ፣ ጢባጢቤ. . .ልመና ሆኗል። የእግዚኦታህ፣ የጩኸትህ፣ የብሶትህ መፍትሄ ቁልፉ አሁንም በአንተው እጅ ነው ያለው። የአንተና የልጆችህ እምቅ ኃይል ነው ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዐብይን ብቅ ያደረገው። ተንፈስ! ብለእ ያጣጣምከውን ፍሬ ለመጨረሻው ድል ማብቃት ይጠበቅብሃልና እራስህን በአገኘኸው አጋጣሚ አደራጅ። የድልህ ዋልታው ድርጅት ነውና። ሀገርህንና ሰንደቅ ዓላማህን እንደምትወድ ሁሉ ድል ማድረግ እንዳለብህም አትዘንጋ። <u>ለሕዝባዊ ድል ሕዝባዊ ድርጅት መሠረቱ ነውና ተደራጅ! አሁንም ተደራጅ!</u>*** ስንል “***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***” ድምጻችንን እናሰማለን።

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**

**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**
**ጥቅምት 8 ቀን 2011 ዓ.ም.** (October 18, 2018)

<u>**ማሳሰቢያ ፡**</u>

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ስልክ፡ (703) 300 4302

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin